# አዋጅ ቁጥር…/2012

## <u>የጥላቻ ንግግርና የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ</u>

ሆን ተብሎ የሚሰራጩ የጥላቻና ሃሰተኛ ንግግሮችን በሕግ መከልከልና መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የጥላቻ ንግግርና የሃስተኛ መረጃ ስርጭት ለማህበራዊ ስምረት፣ ለፖለቲካ መረጋጋት፣ ለሃገራዊ አንድነት፣ ለሰብአዊ ክብር፣ ለብዝሃነትና ለእኩልነት ጠንቅ መሆኑን በመገንዘብ፤

መሰረታዊ መብቶች ላይ የሚጣሉ ገደቦች በሕግ የተደነገጉ፣ በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለውን አላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ፣ተመጣጣኝና በጠባቡ የተበጁ መሆን እንዳለባቸው በመገንዘብ፤

በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### <u>1. አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የጥላቻ ንግግርን እና የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር …/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### <u>2. ትርጉም</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካለሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ "**ንግግር**" ማለት በቃል፣ በጽሑፍ፣ በምሥልና ሥዕል፣ በቅርጻ ቅርጽ እና በሌሎች ተመሳሳይ መንገዶች መልእክትን የማሰራጨት ተግባር ነዉ፡፡

Revised Draft

2/ “**የጥላቻ ንግግር**” ማለት በአንድ ሰዉ ወይም የተወሰነ ቡድን ላይ ያነጣጠረ፣ ብሄርን፡ብሄረሰብንና ህዝብን፣ ሀይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን የሚያበረታታ ንግግር ነው።

3/ “**ሃስተኛ መረጃ**” ውሸት የሆነና የመረጃውን ውሸት መሆኑን በሚያውቅ፣ ወይም መረጃውን የሚያሰራጨው ሰው ካለበት አጠቃላይ ሁኔታ አንጻር የመረጃውን ሃሰተኝነት ሊያውቅ ይገባ ነበር የሚያስብል በቂ ምክንያት እያለ የሚሰራጭ ሁከት ወይም ግጭት የማስነሳት፣ ወይም ጥቃት እንዲደርስ የማድረግ እድሉ ከፍ ያለ ንግግር ነው።

4/ "**ብሮድካስት ማድረግ**” ማለት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ሥርጭት ማድረግ ነዉ፡ ፡

5/ "**ማህበራዊ ሚዲያ**" ማለት ሰዎች መልዕክት ለመለዋወጥ ፤ ትስስር ለማዳበር፤ ሀሳብ ለመጋራት የሚጠቀሙበት በኢንተርኔት አማካኝነት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች መረጃ የሚደርስበት፣ ወይም ማህበራዊ መስተጋብር የሚስተናገድበት መንገድ ነዉ፡፡

6/ “**የህትመት ሚድያ**” ማለት ለህዝብ ስርጭትየተዘጋጀ ማንኛውም የህትመት ወጤት ነው።

7/ "**ሰዉ**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

8/ ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገለጸ ለሴት ጾታ ያገለግላል፡፡

## 3. አላማ

የአዋጁ አላማዎች:

1/ ሰዎች ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብታቸውን ሲጠቀሙ ግጭት ወይም ሁከትን የሚቀሰቅስ ወይም ብሄርን፤ ሀይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ በግለሰብ ወይም በተለየ ቡድን ላይ ጥላቻ ወይም መድልዎ የሚያስፋፋ ንግግር ከማድረግ እንዲቆጠቡ ማድረግ፤

2/ መቻቻልን፣ የዜጎች ውይይትና ምክክርን፣ መከባበርና መግባባትን ማበረታታትና ዲሞክራሲያዊ ስርዐትን ማጎልበት፤

Revised Draft

3/ የጥላቻ ንግግርን፣ የሃሰተኛ መረጃና ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች የውሸትና አሳሳች መረጃዎችን ስርጭትና መበራከትን ለመቆጣጠርና መግታት ነው።

**4. የጥላቻ ንግግር ስለመከልከሉ**

የጥላቻ ንግግርን በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚድያ በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪድዮ ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡

**5. የሃሰት መረጃን ማሰራጨት ስለመከልከሉ**

የሃሰት መረጃን በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚድያ በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪድዮ ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡

**6. ልዩ ሁኔታ**

1/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 እና 5 እንደተጠበቁ ሆኖ አንድ ንግግር እንደ ጥላቻ ንግግር ወይም እንደ ሃሰት መረጃ ተወስዶ ማሰራጨት የማይከለከለው፡-

ሀ) የትምህርታዊ ወይም ሳይንሳዊ ምርምር አካል እንደሆነ፤

ለ) የዜና ዘገባ፤ ትንታኔ ወይም የፖለቲካ ትችት አካል እንደሆነ፤

ሐ) የኪነጥበበ ፣ ትወና ወይም መሰል የስነጥበበ ውጤት ከሆነ፣

መ) የሃይማኖታ አስተምህሮት አካል እንደሆነ ነው።

2/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ንግግር እንደ ሃሰተኛ መረጃ ተወስዶ የማይከለከለው ንግግሩን ያሰራጨው ወይም ያደረገው ሰው የመረጃውን እውነተኛነት ለማረጋገጥ በሱ ሁኔታ ካለ ሰው የሚጠበቀውን ምክንያታዊ ጥረት ያደረገ እንደሆነ ወይም ንግግሩ የጥሬ ሃቅ ዘገባ ወይም ዜና ከመሆን ይልቅ ወደ ፖለቲካ አስተያየትና ትችትነት ያጋደለ ከሆነ ነው።

**7. የወንጀል ተጠያቂነት**

1/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 መሰረት የተከለከለዉን የጥላቻ ንግግር ያደረገ እንደሆነ እስከ ሶስት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር 100,000 ያልበለጠ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2/ በጥላቻ ንግግሩ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ አምስት አመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል።

Revised Draft

3/ ማንኛውም ሰው  በዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 መሰረት ክልከላ የተደረገበትን ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እስከ አንድ አመት በሚደርስ በቀላል እስራት  ወይም ከብር 50,000  ባልበለጠ መቀጮ  ይቀጣል፡፡

4/ የጥላቻ ንግግር ወይም የሃሰተኛ መረጃ ስርጭት ወንጀሉ የተፈጸመው ከአምስት ሺ በላይ ተከታይ ባለው የማህበራዊ ሚድያ ገጽ ከሆነ ወይም በብሮድካስት አገልግሎት ወይም በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ውጤት ከሆነ ቅጣቱ አስከ ሶስት አመት የሚደርስ ቀላል እስራት  ወይም  ከብር 100,000 ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል፡፡

5/ ሃሰተኛ መረጃ በመሰራጨቱ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ ወይም የተሞከረ ከሆነ፣ ሁከት ውይም ግጭት የተከሰተ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል።

6/ በጥላቻ ንግግር ውይም በሃሰተኛ መረጃ ወንጀል መፈጸም ምክንያት   በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት ያልተፈጸመ ወይም ያልተሞከረ ከሆነ፣ ሁከት ውይም ግጭት ያልተከሰተ እንደሆነ እና ጥፋተኛዉን ለማረም የተሻለ ነው ብሎ ሲያምን ፍርድ ቤቱ በእስራት ምትክ የግዴታ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራን በአማራጭ ቅጣትነት ሊወስን ይችላል።

7/ በዚህ አዋጅ የተከለከሉት ተግባራት የተፈጸሙት በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ከሆነ በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተካተቱት በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት የሚደረጉ ወንጀሎችን የተመለከቱ ድንጋጌዎች( አንቀጽ 42-47) ተግባራዊ ይሆናሉ።

## 8. <u>የተቋማትና የአገልግሎት ሰጪዎች ሀላፊነት</u>

1/ ማንኛውም የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት የጥላቻ ንግግርና የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመቆጣጠርና ለመግታት ጥረት ማድረግ አለበት።

2/ ማንኛውም የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት የጥላቻ ንግግርን ወይም የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን የተመለከተ ጥቆማ ሲደርሰው   በፍጥነት ይህን መሰል መልዕክቶችን ወይም ንግግሮችን ከአግልግሎት አውታሩ ሊያስወግድ ይገባል።

Revised Draft

3/ ማንኛውም የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ(1) ና (2) የተንደነገገውን ግዴታውን ለመወጣት የሚያስችለው አሰራርና ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1-3) የተደነገገውን ግዴታ አለመወጣት ሊያስከትል የሚችለው የፍትሃ ብሄር ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች በዚህ አንቀጽ የተቀመጠውን ግዴታቸውን ባግባቡ መወጣታቸውን እየተከታተለ ለህዝብ ይፋ የሚሆን ሪፖርት ያዘጋጃል።

5/ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን የሃሰት መረጃ ስርጭትና ጉዳትን ለመከላከል የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል።

6/ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል።

7/ የተቋማትና የአገልግሎት ሰጪዎች ሀላፊነትን ዝርዝር የሚደነግግ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊወጣ ይችላል።

9. <u>ስለተሻሩ ህጎች</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ 486 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

10. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ-----ቀን----2012 ዓ/ም

**ሳህለወርቅ ዘዉዴ**

**የኢፌድሪ ፕሬዚደንት**

Revised Draft